0920666595

ክፍል 1

የምርጫ ጥያቄዎች (እያንዳንዱ 2 ነጥብ ይይዛል)

1. ከሚከተሉት ውስጥ የክሳሽ ግዴታ ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. በፍታብሄር ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 242 መሠረት የሚጠይቀውን ዳኝነት በግልጽ ማሳየት፡
   ለ. የሚጠይቀውን ዳኝነት በፍ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ/83 መሠረት ማቅረብ።
   ሐ. ግዴታ መኖሩን በፍ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 244 መሠረት ማቅረብ ፡
   መ. ሁሉም መልስ አይደሉም
2. የፍሐብሄር ክርክር መነሻ ሊሆን የሚችለው ምንድን ነው?
   ሀ. ሕግ ነው
   ለ. ውል ነው
   ሐ. ስምምነት ነው
   መ.ሁሉም መልስ ናቸው
   ሠ. መልስ አልተሰጠም

አለሕግ

3. በክስ ማመልከቻ ሲገለጹ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል የሆነው የትኛው?
   ሀ. የክሱ ምክንያት
   ለ. የክስተቱን ጊዜና ሥፍራ
   ሐ.የፍርድ ቤቱን የሥልጣን ክልል
   መ. የፍርድቤቱን የሥረነገር ሥልጣን
   ሠ.ሁሉም መልስ ናቸው።
4. ከሚከተሉት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ድንጋጌ ውስጥ አንዱ በክርክር ሂደት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት አያገለግልም፡
   ሀ.የፍታብሄርሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 ድንጋጌ
   ለ. የፍሥ/ሥ/ሕ/ቁ/41
   ሐ.የፍታብሄር ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/78
   መ.የፍታብሄር ሥ/ሥ/ሐሕ/ቁ/70
   ሠ. ከአንዱ በስተቀር ሁሉም መልስ አይደሉም
5. ከሚከተሉት የፍትሐብሄር ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ ከቼክ ክፍያ ጋር ለተያያዘ ክስ ከሳሽ የሚጠቀሰው ድንጋጌ የሆነው የትኛው ነው?

@Alehig

ሀ.የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 284

ለ. የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 286

ሐ.የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/83

መ. የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ252

6. አቶ ገመቹ በመንግሥት መ/ቤት ለ30 ዓመታት ከአገለገሉ በኋላ የጡረታ መብታቸውን አስከብረው በአቶ አደፍርስ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥረዉ 5 ዓመት ከስድስት ወራት እንዳገለገሉ በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን ለቀቁ። አቶ ገመቹ በአቶ አደፍርስ ፋብሪካ ውስጥ ከአምስት ዓመት በላይ ስላገለገሉ በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት ሀሳብ አላቸው። እርስዎ የሕግ አማካሪና ጠበቃ ቢሆኑና አቶ ገመቹ እርሰዎ ዘንድ ቢመጡ ምን ዓይነት የሕግ ምክር ሊሰጧቸው ይችላሉ? አለሕግ

ሀ. የሥራ ስንብት ክፍያ ብቻ ሳይሆን ያልተጠቀሙበት የዓመት ፈቃድ ወዲ ገንዘብ ተለውጦ ሊከፈላቸው ይገባል ይላሉ።

ለ. ስንብቱ ህገወጥ በመሆኑ በአሠሪ እና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት ተገቢውን ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው እላለሁ።

ሐ. ካሳ እና የሥራ ስንብት ክፍያ የመጠየቅ መብት ቢኖራቸውም፣ እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ በፍርድ ቤት ሊታይ አይችልም እላለሁ።

መ.የጡረታ መብት ስላላቸዉ ጥያቄአቸው ሕጋዊ ድጋፍ የለውም።

7. አቶ ግዛው በአቶ ወንድወሰን ሆቴል ውስጥ በወር 15000 (አሥራ አምስት ሺህ) ደመወዝ እየተከፈላቸው የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ሰራተኛ ይቀጥራሉ፣በህግ አግባብ ያሰናብታሉ። በዚሁ ሥራ ለ9 ዓመታት ሰርተዋል። ከሆቴሉ ባለቤት ጋር ያለመግባባት ስለተፈጠረ እስከመደባደብ ተዳርሰው አቶ ወንድወሰን ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ አቶ ግዛውን ከሥራ አሰናበታቸው። አቶ ግዛው በሕገወጥ የሥራ ስንብት ምክንያት የስራ ስንብትን ጨምሮ የማስጠንቀቂያ እና ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማግኘት አስበው እርሶ ዘንድ ለህግ ምክር ቢመጡ ምን ዓይነት የህግ ምክር ይሰጧቸዋል

ሀ. ከአምስት ዓመት በላይ ስላገለገሉ ጥያቄአቸው ተገቢ ነው።

ለ. ያለማስጠንቀቂያ ስለተሰናበቱ በአሠሪ እና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ክፍያው ይገባቸዋል።

@Alehig

ሐ. አሰሪ ከሰራተኛ ጋር መደባደብ ስሌለበት አቶ ግዛው ወደሥራቸው መመለስ አለባቸው::

መ. ሁሉም መልስ አይደሉም

8. ውል ከሚይዛቸው መሠረታዊ መስፈርቶች መካከል የማይመደበው የትኛው ነው?

ሀ. የተዋዋዮች ቁጥር ወይም መጠን

ለ. የተዋዋዮች መኖሪያ ቦታ

ሐ. የተዋዋዮች የሀብት መጠን

መ. ሁሉም መልስ ናቸው::

9. በውል ህግ ለዋስትና ሁለት ሰዎች በአንድነትና በነጠላ ዋስ ለመሆን ሲፈቅዱ 3 ውል እንደተፈፀመ ይቆጠራል፤ ይህ አባባል ከሚከተሉት ውስጥ ከየትኛው ጋር ይዛመዳል?

ሀ. አንዱ ዋስ ለብቻው ግንዘቡን ለመክፈል መስማማቱን

ለ. ሌላኛውም ሰው ለብቻው የብድር ገንዘቡን ለመክፈል መስማማቱን

ሐ. ሁለቱም በጋራ ገንዘቡን ለመክፈል መስማማታቸውን

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

አለሕግ

10. ወ/ት ፍሬሀይወት በአንድ መንግስት መሥሪ ቤት የእቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ ሆና ለመቀጠር ተያዥ ፈልጋ አቶ ሽፈራው ዋስ ሆነላት:: የአቶ ሽፈራው የወር ደመወዝ 17,000 (አሥራ ሰባት ሺህ) ስለመሆኑ አሰሪው መስሪያ ቤት በደብዳቤ አረጋግጦአል:: ፍሬሀይወት በሁለት ዓመት ቆይታ ጊዜ ዉስጥ የብር 190,000 (አንድ ሙቶ ዘጠና ሺህ)ብር የንብረት ጉድለት ተገኝባት:: አቶ ሽፈራው በገባዉ የዋስትና ግዴታ መሠረት ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍል ከወ/ት ፍሬሀወት አሰሪ መስሪያ ቤት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ደርሶታል:: ከእነዚህ ሀተታዎች በመነሳት ምን ዓይነት የህግ መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ?

ሀ. ግዴታ ከህግና ከውል የሚመነጭ በመሆኑ በፍሬሕይወት መ/ቤት ላይ የደረሰውን የገንዘብ ጉድለት አቶ ሽፈራው መክፈል አለበት እላለሁ::

ለ. የዋስትና ገንዘቡ በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ ዋሱ ተጠየቂ ይሆናል::

ሐ. የዋስትና ግዴታ መጠን በግልጽ ካልተቀመጠ አያስጠይቅም::

@Alehig

መ. የዋስትና መጠኑ ተለይቶ የተገለፀ ቢሆንም እንኳን ወ/ት ፍሬህይወት በሕይወት እያለች አቶ ሽፈራው ሊጠየቅ አይገባም።

11. አቶ በቀለ፣ አቶ ደቻላ እና አቶ ጌታቸው ለአቶ ጎይቶም ገንዘብ የመክፈል የእንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው። ይሁን እንጂ አቶ ጎይቶም ለሶስቱም ባለዕዳዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት ዘንግቶ ለአቶ ጌታቸው ብቻ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በሶስቱም ሰዎች ላይ ግን ክስ መሠረተ። እነዚህን ፍሬነገሮች መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት አባባሎች ውስጥ እውነት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ለእንዱ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ለሌሎቹም እንደተሰጠ ይቆጠራል።

ለ. ማሰጠንቀቂያ ባልተጣቸው ግለሰቦች ላይ ክስ መመስረት አይቻልም።

ሐ. ይህ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ክሱን መዝጋት አለበት።

መ. መልሱ አልተሰጠም።

አለሕግ

12. አቶ አዱኛ እድሜአቸዉ 92 ዓመት ቢሆንም የሰፈር እድር ሊቀመንብር ናቸው። በዚሁ ጊዜ ውስጥ ያላቸውን ቪላ ቤት በወር 45000(አርባ አምስት ሺህ ብር) አከራይተዋል። ለአንድ ዓመት ያህል በየወሩ የኪራይ ገንዘቡን ከሰበሰቡ በኋላ ሀሳባቸዉን ቀይረው ይህ ቪላ ቤት በወር 75000(ሰባ አምስት ሺህ)ይከራያል፣በእድሜ መግፋቴን (መጃጀቴን) ተጠቅመህ ነው ውል ያስፈረምከኝና ውሉ ፈራሽ ነው በሚል እሳቤ ከተከራዩ ከአቶ ሁነኛው ጋር በፍርድ ቤት ለመከራከር ቆርጠዋል። ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት ግን እርሰዎን ማማከር ፍልገዋል። ይህ ጉዳይ እርሰዎ ዘንድ ቢቀርብ ለአቶ አዱኛ ምን ዓይነት የህግ ምክር ይሰጧቸዋል?

ሀ. በፍ/ሕ/ቁ/1710 እና 1808 መሠረት ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ነው።

ለ. አቶ አዱኛ በዕድሜ የገፉ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁ/1771 መሠረት ሊፈጸም የሚችል ውል አይደለም።

ሐ.በ/ሕ/ቁ/1820 መሠረት ራሳቸው አቶ አዱኛ ውሉን ማፍረስ ይችላሉ።

መ.ውሉ ሲመሰረት ምንም ዓየነት ጉደለት ስሌለበት የሚፈርስበት የሕግ ምክንያት የለም።

13. አቶ ሽምሱ ከአቶ ሙስጠፋ ላይ በዱቤ በብር 3,000 የውሃ ማሞቂያ ገዙ። ለመተማመኛም ከአምስት ወር በኋላ የሚመነዘር ይህንኑ የገንዘብ መጠን የያዘ ቼክ ለአቶ ሙስጠፋ ሰጥተዋል። የመክፈያው ጊዜ ሲደርስ አቶ ሽምሱ ገንዘቡ

@Alehig

ለመክፈል አልቻሉም። በዚህም ምክንያት አቶ ሙስጠፋ ቼኩን ለመመንዘር ወደ ባንክ ቢሄዱም የአቶ ሽምሱ ሂሳብ በቂ ሰንቲ የለውም ተብለው ማስረጃ ተሰጥቶአቸው ተመልሰዋል። ከዚህ ጉዳይ በመነሳት እውነት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በእጃቸው ያለው ቼክና የባንክ ማስረጃ ሰነድ በቂ ማስረጃ ስለሆነ ክሱ አዋጭ ነው።

ለ. ቼክ ሀተታ የሌለበት እንደቀረበ የሚመነዘር እጂ የዋስትና ሰነድ ባለመሆኑ አዋጭ ክስ አይደለም።

ሐ. በፍ/ሕ/ቁ/2002 መሠረት በህሊና ግምት ማስረዳት ስለሚቻል ክሱ አዋጭ ነው።

መ. ከብር 500 ብር በላይ ለሆነ ብድር በመሃላ ቃል ወይም በውል ሰነድ ካልሆነ ማስረዳት ስለማይቻል ክሱ የመያዋጣ አይደለም።

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

14. በኢትዮጵያ ውስጥ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የሥራ-ነገር ሥልጣን ለመግንዘብ የሚረዳን ሕግ የትኛው ነው?

አለሕግ

ሀ. የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት

ለ. በ1958 ዓ.ም የወጣው የፍ/ብ/ሥ/ሕግ

ሐ. በ2013 ዓ.ም የወጣው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013

መ. በ1988 ዓ.ም የወጣው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988

ሠ. መልሱ አልተሰጠም።

15. አቶ ይበልጣል የአቶ ይገረም የግል ት/ቤት ለመግንባት የግንባታ ውል ገብቷል። በውላቸዉ ውስጥ ተጨማሪ ሥራዎች ከአጋጠሙ ተጨማሪ ሥራ ስለመኖሩ በጽሁፍ ከቀረበ አቶ ይገረም በ15 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ተጠቅሷል።ሥራው ከተጀመረ በኋላ አቶ ይበልጣል ተጨማሪ ሥራ እንደሚሠሩ ለአቶ ይገረም በጸሐፍ ቢያሳውቋቸውም አቶ ይገረም ግን በውሉ በተመለከተው አግባብ ምላሽ አልሰጡም። አቶ ይበልጣል ተጨማሪ ሥራውን ሰርተው ተጨማሪ ገንዘብ ጠየቁ።አቶ ይገረም የተጠየቀውን ተጫማሪ ብር 35000 ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን ቢቀር ከሚከተሉት ውስጥ እውነት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የተፈረመው ዳበዳቤ በአቶ ይገረም መፈረም ሲገባው ሥልጣን በሌለዉ በላይት ሥራስ ኪያጅ በመሆኑ ጥያቄው ሕጋዊ ውጤት የለውም።

@Alehig

ለ. በፍ/ሕ/ቁ/ 3033-3037 ድንጋጌዎች መሠረት አቶ ይገረም ክፍያውን ለመፈጸም አይገደድም፡፡

ሐ. አቶ ይረገረም ውል የገባው ከአቶ ይበልጣል ጋር በመሆኑ ሥልጣን የሌለለው ሰው አቶ ይገረምን ሊያስገድደው አይችልም፡፡

መ. አቶ ይገረም የነበረዉን ውል በተወሰነ ደረጃ ለማሻሻል ለቀረበ ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ በዝምታ እንደተቀበለው ስለሚቆጠር ገንዘቡን ለአቶ ይበልጣል ለመክፍል ይገደዳል፡፡

16. በአዲሱ የንግድ ሕግ መሠረት እውቅና ያልተሰጠው የንግድ ድርጅት የትኛው ነው?

ሀ. የእንድ ሰው ኩባንያ

ለ. ሆልድንግ ኩባንያ

ሐ. አክሲዮን ማህበር

መ. የሽርክና ማህበር

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

አለሕግ

17. አቶ በላቸው አቶ ውንድይፍራው በሚያሽከረክረው መኪና ተገጭቶ ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር ከታመመ በኋላ ሊድን ባለመቻሉ ሞተ፡፡ የሟች ወራሾች አቶ በላቸው ከሞተ ሁለት ዓመት ከሶስት ወር በኋላ በመኪናዉ ባለንብረት በአቶ አደፍርስ ላይ የጉዳት ካሳ በፍ/ብሔር ሕ/ቁ 2143(1) መሠረት ክስ መሰረቱ፡፡ አርሰዎ የአቶ አደፍርስ ጠበቃ ቢሆኑ፡

ሀ.የደረሰዉ ጉዳት ሳይሆን ሞት በመሆኑ የቀረበዉ ክስና የህግ ድንጋጌው አይገናኝም፡፡

ለ. የሞት አደጋው መነሻ አሽከርካሪው እንጂ አቶ አደፍርስ ባለመሆኑ ሊጠየቅ አይገባም፡፡

ሐ. አቶ አደርፍርስ ቢጠየቅ እንኳን በፍ/ሕ/ቁ/2162 መሰረት ያለአግባብ መበልጸግ ነው፡፡

@Aleh

መ. አቶ አደፍርስ በወንጀል ተጠያቂ ስለሆነ በአቶ አደፍርስ ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ የሚጣና አይደለም።ሠክሱ በይርጋ ይታገዳል።

18. ከሚከተሉት ውስጥ በወንጀል ሕጉ መሠረት የማታለል ወንጀል ተፈጽሚል ለማለት መሟላት ካለባቸው ነገሮች ሊመደብ የማይችለው የትኛው ነው?

ሀ. አጥፊው ሆነ ብሎ አሳሳች ነገሮችን በመናገር ወይም በመደበቅ መጠቀም፤

ለ. ተበዳይ የአጥፊውን እድራጎት እምኖ ሲታለል፤

ሐ. የተገለጸውን በማመን የተፈጸመ ነገር መኖር አለበት፤

መ. ተበዳይ በመታለሉ ምክንያት ያጣው ነገር መኖር አለበት።

ሠ. አታላዩ ማታለል ብቻ ሳይሆን በጎጂ መሳሪያም ጭምር መጠቀም አለበት።

ረ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ

19. አቶ አጁሉ ኢትዮጵያዊ ነው። ለትምህርት ጉዳይ አሜሪካ ሂዶ አንዲት አሜሪካዊት አግብቶ እዚያዉ መኖር ጀምሮ በመኪና አደጋ ሞተ። ጋምቤላ የራሱ ቤት ነበረው። ከተፋቱ ሶስት ዓመት ያለፈ ሚስት ነበረችው። ዳሩ ግን ልጅ አልወለዱም።ከሚከተሉት የአቶ አጁሉ ወራሽ የሚሆነው ማን ነው?

ሀ.የተፋቱት የቀድሞ ሚስቱ

ለ.አሜሪካ ሂዶ ያገባት ሚስቱ

ሐ. ወዳታች የሚቆጠሩ ተወላጆች

መ. መልሱ አልተሰጠም

አለሕግ

20. አዲሱን የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ከቀደመው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ልዩ የሚያደርገው የትኛው ነው?

ሀ. አዲሱ አዋጅ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለው አገላላጽ ትርጉም የሰጠ መሆኑ፤

ለ. አዲሱ አዋጅ የመጨረሻ ውሳኔ ለሚለው ሀረግ ትርጉም የሰጠ መሆኑ፤

ሐ. የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የማዛት ሥልጣን በግልጽ ያስቀመጠ መሆኑ፤

መ. ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን መስጠቱ

ሠ. ከመ በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው።

@Alehig

ክፍል 2

ጉዳይ አንድ (20%) የከርከር ጉዳዮች (40%)

አውቶ ኢትዮጵያ የሚባል መኪና አምራች ድርጅት ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ የቤት መኪኖችን በማምረት በኢትዮጵያ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውጭ በማከፋፈል ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው። ሀገሬ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ደግሞ ከአውቶ ኢትዮጵያ መኪኖችን እየተረከበ ለተጠቃሚዎች የሚሸጥ ድርጅት ነው። አቶ አውላቸው ደቻሳ ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም በተደረገ የመኪና ሽያጭ ውል አንድ የቤት መኪና ከሀገሬ ላይ በብር 2,500,000.00 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር)ገዛ።

አቶ አውላቸው ደቻሳ ጥር 25 ቀን 2014 ዓ.ም ይህንን መኪና እያሽከረከረ ወደ ደብረብርሃን ከተማ በመሄድ ላይ እያለ ሸኖ ከተማ (አሮሚያ ክልል) ሲደርስ ነዋሪነታቸው የደብረብርሃን ከተማ የሆኑ አራት ግለሰቦች (ማለትም አቶ ዳምጠው ጌራወርቅ፣ አቶ ገመቹ ደስታ፣ አቶ ተድላ ሃጎስ እና ወ/ሮ ባህርነሽ አዳሙ) በነጻ ያሳፍራቸው ዘንድ ጠየቁት። እርሱም ፈቃደኝነቱን ገልጾ እነዚህን ግለሰቦች ምንም ከፍያ ሳይጠይቅ (በነጻ እንደሚወስዳቸው ገልጾ) መኪናው ላይ አሳፈራቸው። ነገር ግን አቶ አውላቸው ደቻሳ ከሸኖ ከተማ ተነስቶ 5 ኪሎሜትር እንደተጓዘ መኪናው ከመንገድ ወጥቶ ተገለበጠ። በዚህም ምክንያት ሹፌሩን ጨምሮ በሁሉም ተሳፋሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

አለሕግ

የአደጋው ምክንያት ምን እደሆነ ለማወቅ በተደረገው ቴክኒካዊ ምርመራ እንደተረጋገጠው አደጋው ሊደርስ የቻለው የመኪናው መሪ ችግር ስላለበትነው። አቶ ደቻሳ የገዛውን ተመሳሳይ መኪኖችን የገዙ ሌሎች ግለሰቦችም መኪኖቻቸው የመሪ ችግር እንዳለባቸው ቅሬታ በማቅረባቸው በማቅረባቸው መኪኖቹን ያመረተው ድርጅት እነዚህ መኪኖች ይመልሱለት ዘንድ ጥሪ አቅርቧል። መኪኖቹን ያመረተው ድርጅት መኪኖቹ ይመለሱለት ዘንድ ጥሪያ ቀረበው እራሱም ባረደገው የቴክኒክ ምርመራም የመኪኖቹ መሪ ከፍተኛ የሆነ ችግር ያለበት መሆኑን ስላረጋገጠ ነው።

@Alehig

ከላይ በጠቀሰው የመኪና አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰባቸው አራቱ ግለሰቦች (ማለትም አቶ ዳምጠው ጌራወርቅ፣ አቶ ገመቹ ደስታ፣ አቶ ተድላ ሃጎስ እና ወ/ሮ ባህርነሽ አዳሙ) ለጉዳቱ ኃላፊነት ባለበት ግለሰብ ወይም ድርጅት ላይ ክስን መመስረት የጉዳት ካሳ ማግኘት እንዳለባቸው ውቅርጥ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል።

ጥያቄዎች

1. በመኪና አደጋው ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች የጉዳት ካሳ ለማግኘት በማን ላይ ክስ ቢመሰርቱ ያዋጣቸዋል? ለምን? አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ይተንትኑ። (10%)
2. አደጋ የደረሰባቸው አራቱም ግለሰቦች ካሳ ሊከፍለን/ሊከፍሉን ይገባል በሚሉት/በሚሏቸው ሰው ወይም ሰዎች ላይ በአንድነት ክስ ለመመስረት ይችላሉን?ለምን? አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ይተንትኑ።(10%)

ጉዳይ ሁለት (20%)

አለሕግ

አቶ ጎሞራው ደላለኝ ወንድሙ አቶ ውቃው ደላለኝ በሰው እጅ ስለተገደለ ሁልጊዜም በሕይወቱ ደስተኛ አይደለም። አቶ ውቃው ደላለኝን ሰኔ 13 ቀን 1976 ዓ.ም የገደለው አቶ እጅጉ ባንተይርጉ ሲሆን፣ አቶ እጅጉ አቶ ውቃውን ከገደለ ጀምሮ በሽፍተነት ሲኖር ቆይቶ እርጅና እየተጫጫነው ሲመጣ ወደ ትውልድ ቦታው ተመልሶ ልጆቹ በሠሩለት ጎጆ ውስጥ መኖር የጀመረው ከመጋቢት 2012 ዓ.ም ጀምሮ ነው።አቶ እጅጉ የሚኖረውም በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ በደብረሲና ወረዳነው።

አቶ ገሞራው አቶ እጅጉን ባየ ቁጥር ንዴቱ እና ብስጭቱ ከመጠን በላይ ይሆናል። አቶ ጎሞራው "የወንድሜን ገዳይ ላልገድል በማርጀቱ ከፍተኛ ፀፀት ይሰማኛል፣ የወንድሜን ገዳይ ገድዬ ዛሬውኑ ብሞት አይቆጨኝም ነበር።"በማለት ቁጭቱን ይገልጻል።አቶ ገሞራው የ26 ዓመቱን የሚች ወንድሙን ልጅ (ወጣት ቀለመወርቅን)ግንቦት 14 ቀን 2013 ዓ.ም ወደቤቱ በመጥራት "አሁን የእኔ ወንድም ልጅ ወለደ ይባላል? አሁን አንተም ከወንድ ትቆጠራለህ? ከአባትህ ገዳይ ጋር አብረህ የምትኖር አንተ ምን ሰው ነህ! እንዳንተ ዓይነቱን ልጅ ከመውለድስ ማስወረድ በስንት እጅ ይሻላል!" በማለት የስድብ እና የተግሳጽ ናዳ አወረደበት። አቶ ጎሞራው ቀጠል አድርጎም "የአባትህን ገዳይ ብትገድልልኝ በባንክ

@Alehig

ያስቀመጥኩትን 2,000,000.00 ብር (ሁለት ሚሊዮን ብር) በሽልማት መልክ አሰጥህ ነበር" አለው።

ወጣቱ ቀለመወርቅም የአንቱን ሰድብ እና የሰጠኃ ተሰፋ ምክንያት በማድረግ የአባቱን ገዳይ ለመግደል የካቲት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 1:30 ከመንግሥት ለአካባቢ ጥበቃ የሰጠውን ከላሽንኮቭ መሳሪያ በመያዝ ወደ አቶ እጅጉ ቤት ሄደ። አቶ ቀለመወርቅ አቶ እጅጉ ቤት እንደ ደረሰ አቶ እጅጉን አላገኘውም። ነገር ግን እጅግ ውብ የሆነችው የ19 ዓመቷ የአቶ እጅጉ ልጅ ወ/ሪት ፈትለወርቅ እጅጉ እቤት ተቀምጣ አገኛት። አቶ ቀለመወርቅም ይችን መልክ መልካም ልጅ ሲያይ በውበቷ ከመጠን በላይ ተማርኮ አቶ እጅጉን የመግደል ሀሳቡን በመተው ፈትለ ወርቅን ሚስት ለማድረግ በማሰብ ይህንኑ ሀሳቡን ለእርሷ እና ለእናቷ በመግለጽ እንዲትከተለው ጠየቃት። ፈትለወርቅ ግን ፈቃደኛ ልትሆን አልቻለችም። በዚህም ምክንያት አቶ ቀለመወርቅ የያዘውን መሣሪያ በፈትለ ወርቅ ላይ ደገነባት። ፈትለወርቅም ከፍተኛ ፍርሃት ስላደረባት ቀለመወርቅን ተከትላ ሄደች። ከእንድ ሳምንት በኋላ አቶቀለመ ወርቅ ወደ እጅጉ ቤት በጣም የተከበሩ እምስት ሽማግሌዎችን ላከ። አቶ እጅጉም በእርሱ እና በአቶ ቀለመ ወርቅ ቤተሰቦች መካከል የነበረውን ጥቁር ደም ለማድረቅ በማሰብ ፈትለወርቅ ከወጣቱቀለመ ወርቅ ጋር በትዳር ብትቀጥል ቅሬታ እንደሌለው ገለጸ።ስለሆነም ሐምሌ 11 ቀን 2013 ዓ.ም አቶቀለመወርቅ እና ው/ሪት ፈትለወርቅ በባህላቸው መሠረት ጋብቻቸውን ፈጽመው በትዳርአብረው እየኖሩነው። ምንም እንኳን ቀለመወርቀበ ወ/ሪትፈትለወርቅ ውበት በእጅጉ ተማርኮ ከፈቃዷ ውጭ ወደ ቤቱ ቢወስዳትም፣ ጋብቻ እስከሚፈጽሙ ድረስ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አልፈጸሙም ነበር።

አለሕግ

ጥያቄዎች

2.1. አቶ ጎሞራው እና ወጣት ቀለመወርቅ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል ለማለት ይቻላልን?ለምን? ተገቢውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ (ዎች) በመጥቀስ በሚገባ ይተንትኑ።(10%)

2.2. ከላይ የቀረበውን ሀተታ መሠረት በማድረግ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል የሚስብል ምክንያትከተገኘ የወንጀል ክሱየሚታየው በክልል ፍርድ ቤት ነው ወይስ በፌደራል ፍርድቤት ነው?ለምን? ተገቢውን የሕግ ድንጋጌ (ዎች) በመጥቀስበ ሚገ ይተንትኑ።(10%)

@Alehig

0920666595

ክፍል 3

የጽንሰ ሐሳብ ጥያቄዎች (20%)

በዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር የመንግሥት ሥልጣን የተከፋፈለ (separation of power) እንደሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን አንዱ የመንግሥት አካል ሌላውን የመንግሥት አካል ይቆጣጠራል።

አለሕግ

ሀ) የመንግሥት የሥልጣን ክፍፍል (separation of power) ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያብራሩ። (10%)

ለ) አንዱ የመንግሥት አካል ሌላውን የመንግሥት አካል የሚቆጣጠርበት እና ሚዛን የሚጠብቅበት ሥርዓት (check and balance) ምን እንደሚመስል ያብራሩ። (10%)

@Alehig